# መጽሐፍ ቅዱስ

## የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

፨ ፨ ፨ ፨ ፨


**ዲጂተል ኤዲሽን ፲፱፻፺፱**

**በዲርክ ሮክማንና ፍሬዘውድ ተክሉ**

**DIGITAL EDITION BY DIRK RÖCKMANN AND FREZEWD TEKLU 2006**

**ETHIOBIBLE MINISTRIES - WWW.ETHIOBIBLE.ORG**

Release 1.0


## የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር


መጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።



**COPYRIGHT STATEMENT:**

DIGITAL EDITION OF THE REVISED AMHARIC BIBLE (2006) | PRINTED VERSION BY UNITED BIBLE SOCIETIES (C)1962| E-TEXT IN TRANSLITERATED SIL-ASCII FORMAT BY LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION 1994 | UNICODE UTF-8 TRANSFORMATION AND XML-TAGGING BY DIRK RÖCKMANN 2003 | XSLT-TRANSFORMATION AND READER FORMAT BY DIRK RÖCKMANN 2006 | WITH KIND PERMISSION OF THE BIBLE SOCIETY OF ETHIOPIA | EVERY NON-COMMERCIAL WORK USING THIS DATA IN ANY FORM MUST FULLY INCLUDE THIS COPYRIGHT STATEMENT! | EVERY COMMERCIAL USE OF PARTS OR THE COMPLETE DATA IN ANY FORM NEEDS WRITTEN PERMISSION OF THE BIBLE SOCIETY OF ETHIOPIA AND DIRK RÖCKMANN (WWW.NT-TEXT.NET,WWW.ETHIOBIBLE.ORG)! ALL RIGHTS RESERVED!

# የዮሐንስ መልእክት 2

፨ ፨ ፨

## ምዕራፍ 1

1-2፤ በእኛ ስለሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ስለሚሆን እውነት፥ እኔ ሽማግሌው በእውነት
ለምወዳቸውና እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ደግሞ ለሚወዱአቸው
ለተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ፤ 3፤ ከእግዚአብሔር አብና ከአብ ልጅ ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር ይሆናሉ። 4፤ ትእዛዝን
ከአብ እንደ ተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ አንዳንዶችን ስለ አገኘኋቸው እጅግ
ደስ ብሎኛል። 5፤ አሁንም፥ እመቤት ሆይ፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ፤
ይህች ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ አዲስ ትእዛዝን
እንደምጽፍልሽ አይደለም። 6፤ እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤
ከመጀመሪያ እንደ ሰማችሁ፥ በእርስዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት። 7፤ ብዙ
አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ
የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው። 8፤ ሙሉ ደመወዝን
እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። 9፤ ለሚወጣ ሁሉ
በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር
አብና ወልድ አሉት። 10፤ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ
በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ 11፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው
ይካፈላልና። 12፤ እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም
ልጽፈው አልወድም፥ ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ አፍ
ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። 13፤ የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላምታ
ያቀርቡልሻል።